# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

**ኢትዮጵያችን ልዩ ዕትም ቅጽ 1 ቁጥር 3** **የካቲት ፳፱ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ.ም.**


## ማርች 8 የኢትዮጵያ ሴቶች የቃልኪዳን ቀን

ለመጀመሪያ ጊዜ እ.አ.አ. በ1911 በጀርመን፣ በአውስትሪያ፣ በዴንማርክና በስዊዘርላንድ የተከበረው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ማርች 8 በእኛ አቆጣጠር የካቲት 29 እነሆ 106 ዓመቱ። ሴቶች በሴትነታቸው ዝቅ ተደርገው በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎአቸው የሚደርስባቸውን አድሎና የወንድ የበላይነትን ለመቋቋምና መብታቸውን ለማስከበር ድምጽ ያሰሙበት ዓለም አቀፋዊ የትግል ቀን 106ኛ ዓመት ማርች 8, 2017። በአጠቃላይ ሴቶች በፆታቸው ለሚደርስባቸው አድልዎ ድምጻቸውን ለማሰማትና የፆታ እኩልነት ተግባራዊ ይሆን ዘንድ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሰባሰቡበትና ትግላቸውም ዓለም አቀፋዊ አንድነት ይኖረው ዘንድ የተጀመረ ክብረ ባህል። ማርች 8 (የካቲት 29)።

የኢትዮጵያ ሴቶች ይህንን ዓለም አቀፍ ባህል የየካቲት 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ አብዮት ተገን አድርገው ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ አክብረዋል። ሴቶችን በማጀት አሥሮ ያስቀረው የባላባት ሥርዓት ላይ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመጽ የሴቶችን ጥያቄ ይዞ ብቅ ማለት ብቻ ሳይሆን ሴቶችን የትግሉ ተሳታፊና አንቀሳቃሽ ሞተር አድርጓል። ሴቶች በእውቀትም ሆነ በችሎታ እንዲሁም በአመራር ብቃታቸው ከወንድ እኩል ብቻ አይደለም ልቀውም ቢታዩ በሥርዓቱ ተንቀውና ተገፍተው ኖረዋል። እንደማንኛውም ዜጋ ከሚደርስባቸው አስከፊ ጭቆና በደልና መብት እረገጣ በተጨማሪ በሴትነታቸው ብቻ የሚደርስባቸውን በደልና እንግልት ለማሸነፍና ማንነታቸውን ለማሳየት ያልታከተ ጥረትና ተጋድሎ ማድረጋቸውን የትላንት ታሪካቸው ይመሰክራል።

“አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” ለ106ኛው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን እንኳን አደረሳችሁ እያልን እራሳችንን ለሀገርና ለሕዝብ ይፋ ባደረግን የመጀመሪያው አጋማሽ ዓመት፤ ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ስንዘክር በሀገራችን የእናቶችንና የሴቶች እህቶቻችን መከራና ሰቆቃ ከሌላው የኅብረተሰብ ክፍል ጋር ተያያዥነት ቢኖረውም ይበልጡን ትኩረት ለሴቶቻችን በመስጠት ነው። ከግፉ ክምር ሥር የዕምባቸው ፏፏቴ ፊታቸውን የጠባበሳቸውን እናቶችና እህቶች ሰቆቃ እየተጋራንና ውስጣችን እያለቀሰ ነው። ሴቶች ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ብሎም ለነፃነት ተጋድሎው ቤተሰባዊ ሕይወት ይሰጡት ዘንድ በማሳሰብ ነው።

የዘንድሮውን ማርች 8 ስናስታውስ የኢትዮጵያ ሴቶች እንግልት ዛሬም አለማብቃቱን እየገለጽን ነው። ጀርባዋ ለሸክም፣ ጉልበቷ ለመፍጨት፣ እጆቿ ለወቀጣ፣ እግሮቿ ለጠጠር የተዳረገች እናት መከራዋ ዛሬም አላበቃም። በድህነት አቅሟ ያሳደገቻቸው አበባዎቿ በስደት፣ በእስርና እንግልት እየተሰቃዩ ሞት ሲቀማት ዓይኖቿ ያላቋረጠ የዕንባ ምንጭ መሆናቸውን በማስረገጥ ነው። አቤቱ ኢትዮጵያ! የእናቶች ዕምባ ይብቃ እያልን ነው።

ለአለፉት 40 ዓመታት የሀገራችን ታሪክ ሰቆቃንና መከራን እያንከባለለ እዚህ አድርሶናል። እኛ ላይ ሲደርስ ታሪክ ዕምባ ሆኗልና “ዕምባ እራሱን ይደግማል” ቢባል የእናቶቻችን ያላቋረጠ ልቅሶና ሰቆቃ ለመመስከር ነው። የደርግ ዘመን የእናቶች ዕምባ ሳይደርቅ የወያኔው ተደገመ። የደርግ ቀይ ሽብር፣ በ1997ቱ ምርጫ ሕፃን ሽብሬዎችን ቀጥፎ አስለቀሰ፣ “ድምጻችን ይሰማ” ጩኸቶች እስላምና እምነት ተከታይ ወንድምና እህቶቻችንን እምሽክ አድርጎ በላ፣ ኢሬቻ ባህላችን ወጣቶችን ከገደልና ከባህር አስቀረ። “ደማችሁ ደማችን” ለገዳዮች ዘፈን፣ ለእናቶች ዕምባ፣ ለጨካኞች ፈንጠዝያ ሆነ። ወልዶና አሳድጎ ለገዳይ ሲሳይ።

ዛሬ ማርች 8ን ስናከብር በአለፉት 40 ዓመታት ለተፈራረቁት ጨካኝና ገዳይ አገዛዞች መፍትሄው ጠንክሮ መታገል መሆኑን በማሳሰብ ነው። አንድ ትውልድ ያጠፋን የደርግ ጦረኛ ሥርዓት ሀገርና ሕዝብ ሊያጠፋ ያሰፈሰፈና ጦሩን የሳለ/ያሾለ የወያኔ/ህወሀት አገዛዝ ተክቶ፤ ሰቆቃው በየቦታው ቢበረታም ትግሉ ጥንካሬን ይጠይቃልና እናትና እህቶቻችን ለትግሉ መላ በሉ እንላለን። ሀገራችንን ኢትዮጵያ ሊያፈርሳት ካሰፈሰፈው ወያኔ አላቀን በሕዝብ አንድነት ላይ የተመሰረተች ሀገር እውን ለማድረግ ትግሉ ዕምባ ሳይሆን ደም ይጠይቃልና ክብር ለኢትይዮጵያ ብለን እንነሳ።

በኢትዮጵያ ሀገራችን ሴቶች ከአመራርነት ጀምሮ ጉልህ ሚና እንደነበራቸው ጥንት ንግሥት ማክዳ፣ በአፄ ምኒልክ ዘመንም ንግሥት ዘውዲቱ የታሪክ ምስክር ናቸው። የዐድዋ ድል በጀግኖች እናቶቻችን ስንቅና ትጥቅ አቅራቢነት ብቻ ሳይሆን፤ በመላና ብልሀት መገኘቱ እቴጌ ጣይቱን ከድሉ ጫፍ ያስቀምጣል። የወ/ሮ ሸዋረገድ ገድሌ አርበኝነት ፋሽስት ጣሊያን ላይ ለተቀዳጀነው ድል ከፍተኛ አስተዋጽዎ አበርክቷል። በዘመነ ደርግ የኢትዮጵያ ሴቶች ከማንም ባላነሰ ለሕዝብ መንግሥት ምስረታና ለዴሞክራሲያዊ መብት ተግባራዊነት ባደረጉት ተጋድሎ መስዋዕት ሁነዋል። “ልቅሶ አልሻም” ብለው ለሀገርና ሕዝብ ደህንነት ወደ ትግል አደባባይ የወጡ እህቶች አሳዛኝ መስዋዕትነት ከፍለዋል። “አመጻህ አመጼ፣ ሀገርህ ሀገሬ” ብለው ለትግል በረሃ የረገፉ እንስቶች ቀላል አይደሉም።  ታሪክ ሊያስታውሳቸው የሚችለው ያልተቋጨው ጉዞ ቀጣይነት ሲኖረው ነው። ያልተመለሰው የሕዝብ መንግስት ዛሬም ሲጠየቅ ነው። የዴሞክራሲ መብት፣ የዜግነት መብት፤ የሀገርና ሕዝብ ሀብት ሲሆን ነውና ሩጫችሁን ያልጨረሳሽሁ፣ ከግባችሁ ያልደረሳችሁ ሴቶች እህቶቻችን የትግሉ እማወራ መሆን ይጠበቅባችኋል።

የህወሀት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በተለይ በከተሞች ሴሰኝነትን፣ ሴተኛ አዳሪነትን፣ የመንገድ ዳር ተቁለጭላጮች ሴቶችን በማበራከቱ ዋናውን ዕድገት ያስመዘገበ ነው። የኢትዮጵያ ሴቶች ዕጣ ፈንታ ከዝሙትና ሴሰኝነት እንዳይዘል በቀየሰው ፖሊሲ የሀገሪቷ ግማሽ ኃይል የሆኑትን ሴቶች እያሽመደመደ ሀገርና ትውልድ እየገደለ ይገኛል።

የወያኔ/ህወሀት አገዛዝ በየቦታው በአሰማራቸውና በአመቻቸላቸው ደላሎች በየጊዜው ወደ አረቡ ሀገር የሚጋዙ ሕፃናትና ወጣት ሴቶች ቀላል አይደሉም። በየበረሃውና በየባህሩ ሰምጠው ከሚቀሩት የተረፉት ከፎቅ መወርወር፣ በአሲድ መጠበስ የሚጠብቃቸው ተስፋ መሆኑን ከተገነዘብን ዓመታት አስቆጥሯል።

በወያኔ/ህወሀት አገዛዝ ባለሥልጣናት ተራ የወሲብ ፍላጎትና ሴሰኝነት ማርኪያ የሚሸጡትና የሚቸረቸሩት እህቶቻችን አሳዛኝ ጉዳይ “ወይ ዘመን” በማለት ከንፈር የሚመጠጥበት ሳይሆን ወገብን ጠበቅ አድርጎ መፋለምን የሚጠይቅ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። እጅግ የተንሰራፋው ያለአቻ ጋብቻና ሕፃናትን አስገድዶ መድፈር የአገዛዙ የረቀቀ ትውልድ የማቀጨጭና የሀገር ተስፋዎችን የመቅበር ዕቅድ ውስጥ የሚካተት ኢትዮጵያን የማዳከም ወያኔያዊ ስልት ነው። እነኚህንና መሰል ተንኮሎችን ለማክሸፍና በሕዝባዊ ድል አድራጊነት ለመወጣት የሴቶች እህቶቻችን በትግሉ ተሳትፎና አመራር መስጠት ይጎላ ዘንድ ማርች 8 ሲያከብሩ ቃል የሚገቡበት ቀን መሆን ይገባዋል እንላለን።

“ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” ዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን ስናስታውስ በሀገራችን ኢትዮጵያ በሴቶች እህቶቻችን ላይ የሚደርሰውን አስከፊ ጭቆናና በደል በማሰብ ነው። ያለ ዕድሜ ጋብቻ በሚደርስባቸው ስቃይ፣ አስገድዶ መድፈር፣ መጥለፍ፣ አካሏን ማበላሸት፣ ከአቅም በላይ ለሆነ የጉልበት ሥራ መዳረጋቸው፣ በዝሙት አዳሪነት አካልን በመሸጥ የሚደርስባቸውን እንግልትና በሽታ በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት በመካከለኛው ምሥራቅ በተለይ በአረቡ ዓለም እየደረሰባቸው ያለውን የመረረ እንግልትና መከራ በማስታወስ ነው።

ማርች 8 ሴቶች እህቶቻችን ለፆታ እኩልነት ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጆች የዜግነት መብት ማንነታቸውን የሚያሳዩበት መሆን ይገባዋል። ሴቶች እህቶቻችን የትግሉ ቀዳማይ እመቤት በመሆን ኢትዮጵያንና ሕዝባቸውን ከአምባገነንና ዘረኛ አገዛዝ መዳፍ ሥር ለማላቀቅ ቁርጠኝነታቸውን የሚያሳዩበት ቀን መሆን ይገባዋል። ሴቶች እህቶቻችን “ማርች 8 ለሀገር አንድነት፣ ለዴሞክራሲ መብት” ብለው ባህሉን ክብር በመስጠት የቃልኪዳን ቀን ሊያደርጉት ይገባል ስንል ከ“አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” ድምጻችንን እናሰማለን። እማሆይ! እህት ሆይ! “መላ አይጠፉም ከጅሽ” እንላለን።

**ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ማርች 8 የትግል ቀን!!!**

**በሴቶች ተሳትፎ ሕዝባዊ ትግሉ ግቡን ይመታል!!!**

**ግጥሙን በቀጣዩ ገጽ ያንብቡ።**

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**
**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**
**“አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ”**

የካቲት 29 ቀን 2009 ዓ.ም. (March 08, 2017)

# መላ አይጠፋም ከእጅሽ

እህት ዓለም. . .

አንቺ የሕይወት ብርሃን
መሠረተ ሔዋን
ቀና በይ ተዘጋጅ
ተረከቢ ግዳጅ።
መላ ካንቺ አይጠፋም
በርቺልን እህት ዓለም
ትግል ስሪ እታለም።
ከድርብ ጭቆና መላቀቅን ይዘሽ
የፆታ በደልን እሽሩሩ እንዳልሽ
የተበተበሽን ዘረኛ ሰንሰለት
በጥሰሽ ለመጣል ሆነሽ በአንድነት
ከዚያም በላይ ዘልቀሽ
ሀገርን አስበሽ
ለወገን እንድትደርሽ
ተነሽልን ታጥቀሽ
መላ አይጠፋም ከጅሽ።

እታለም . . .
ተነሺ፣ ታጠቂ በርቺና
አሟሺው ትግሉን፤ ከመሃል ግቢና
እምዬን በይና፤ ኢትዮጵያን ካሉት
ማህተሟ እንዳይወልቅ፤ የእምነት ሰንሰለት
እንድትጮኺለት፤ የሕዝብን ብሶት
እንድንደርስላት፤ ለዛች የደም መሬት
ሥጋ ለሌላቸው፤ ለተራቡ ሕፃናት
ለእኛ ለአዛውንቶች፤ በፀሎት ላሉቱ
ለሕፃናት ወጣቶች፤ በአልጋ ለቀሩቱ
መፍትሄ ትሆኝለሽ
እታለሜ ተነሽ
የትግሉ ወጌሻ
መላ አይጠፋም ከጅሽ።

እታለም. . . እህት ዓለም. . .
ብንገፋው፣ ብንለው
ብንዘል፣ ብንፈርጠው
ዝግ ብንል፣ ብንሮጠው
ብረቱን ባነሳው፣ መልሼ ባወርደው
ሰላምን ብፈልግ፣ እጄን ባጣምረው
ስደት፣ እሥር፣ ስቃይ ሆነኮ መቋጫው
ጥይት ነው ሚዘንበው።

በመላ ኢትዮጵያ፤ ጨለማ ሲነጋ
ብርሃን እንዲወጣ፤ ሌት ተቀን ብንፈጋ
ያገራችን ውሉ፤ መቋጫ የመፍትሄው
አልጨበጥ ብሏል፤
ጉም ሆኖ ይበናል።
እታለም ጉራ በይ፤ ከትግሉ አደባባይ
ምስጢሩ ካንቺ ነው፤ ያገራችን ራዕይ።

እታለም. . . እታለም . . .

እጅ ለጅ ተያይዘን
ባንድ ላይ ለመጓዝ
እኛስ ተስኖናል፤ ያላባራ መዘዝ
በአንድ ሀገር፤ በአንድ ቤት
ሲሳነን መስማማት።

ሀገራችን ብለን፡
ሀገር ስትረሳን
ሕዝባችንን ብለን፡
ማየቱ ሲሳነን
ራዕያችን ብለን፡
ዕልም ቅዠት ሲወረን
ተልዕኮአችን ብለን፡
መልዕቁ ሲጠፋን
ዓላማችን ብለን፡
ሰንደቁ ሲረሳን
እታለም. . . ግቢበት
ቀምሚ ትግሉን፡
ጠንስሺ እርሾውን፡
ውቀጭ ከሃዲውን፡
ቀንጥሺ አድርባይ ባንዳውን፡
አበጥሪ ለይው፤ እንክርዳድ አታላዩን
ፍጪና አድቅቂው፤ ወያኔ ሌባውን።

እሽሩሩ ብለሽ፤ ሁሉንም በዘዴ
በእጆችሽ ጨብጠሽ፤ ጋሻና ጎራዴ
መሃላችን ግቢ፤ እንደው ዘራፍ ብለሽ
እታለም ተነሺ መላ አይጠፋም ከጅሽ።
. . . እታለም ተነሺ መላ አይጠፋም ከጅሽ።

«ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ»
ዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን ማርች 8 ምክንያት በማድረግ።
የካቲት 29 ቀን 2009 ዓ.ም.
March 08, 2017

**<u>ማሳሰቢያ ፡</u>**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «***ኢትዮጵያችን***» ልሳን በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org

ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com

ምስለ ገጽ : 1HɪH Ethiopiachen